# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውሃ፣ የመስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር

## ለመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ተቋማት ክትትል፣ ጥገና እና መለዋወጫ አቅርቦት ሥራዎች ላይ በሴቶችና በወጣቶች የሚመራ ኢንተርፕራይዞች የማደራጀት ፕሮጀክት የምክክር መድረክ

ሐምሌ 7 እና 8 ቀን 2008 ዓ.ም

# መግቢያ

- ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2025 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ የመሰለፍ ራዕይ ሰንቃ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች፡፡ ስለሆነም ሁሉም የሃገሪቱ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስተራቴጂዎችና ዕቅዶች ይህን ታላቅ ራዕይ ዕውን ከማድረግ አኳያ ያላቸው ፋይዳ እየተቃኘ በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡
- **በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ(GTP2)**
  - በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትኩረት ከተሰጣቸው የመሰረታዊ አገልግሎት የልማት አውታሮች መካከል የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦት አንዱ ነው፣
  - በገጠር 25 ሊትር በነፍስ ወከፍ በቀን በ 1 ኪ.ሜ ራዲየስ በ2007 መጨረሻ ካለበት ከ59 % - 85% እንዲሁም የከተማውን ህብረተሰብ ንፁህ፣ በቂ እና ዘላቂ የመጠጥ ውሃ ሽፋን በነፍስ ወከፍ በቀን **40 ሊትር እስከ 100 ሊትር** የከተሞችን የዕድገት ደረጃ መሠረት በማድረግ) በ2007 ዓ.ም መጨረሻ ከነበረበት **51%** በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2012 ዓ.ም) ወደ **75%** በማሳደግ፣
  - አጠቃላይ የሀገሪቱን የመጠጥ ውሃ ሽፋን በዕቅድ ዘመኑ **መጨረሻ ከ58 % ወደ 83%** ማሳደግ፣
  - እንዲሁም የውሃ ተቋማት ብልሽት ከነበረበት **15.5 % ወደ 7 %** ለመቀነስ ታቅዷል፣
  - በመሆኑም የንፁህ መጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጅን አገልግሎትን በዕቅዱ መሠረት ለህብረተሰቡ ለማድረስ እንዲቻል የዘርፋን ልማት በተለያየ መልኩ መደገፍ ያስፈልጋል፣
  - ስዚህም እንደ አጋዥ የሚሆኑትን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ማስፋፋት ሲሆን በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ግንባታ ጥገናና የመለዋወጫ አቅርቦት ሥራዎች ላይ ማሳተፍ፣

# የማንዋሉ አስፈላጊነት

- የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ልማት ከፍተኛ የፋይናንስና የሰው ኃይል እንዲሁም የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፣
- የዘርፉን ልማት ለማስፋፋት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማደራጀት፣ በማሰልጠንና በማሳተፍ አነስተኛ ወጪን የሚጠይቁ ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋትና መጠቀምን ይጠይቃል፣
- የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት፣ የብልሽት መጠን ለመቀነስና የመለዋወጫ አቅርቦትን ተደራሽ በማድረግ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ሽፋንን በማሳደግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥና ዘላቂ አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል፣
- በተጨማሪም አሁን ካለው ፍጥነት በበለጠ ልማቱን ለማካሄድ የሚያስችሉ ስልቶችን በመንደፍ፣ በዘርፉ ተወዳዳሪና ውጤታማ የሆኑ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መፍጠር ብሎም ለወደፊቱም ብቁና በገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ተቋራጮችን ለማፍራት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን መደገፍ ያስፈልጋል
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂን መነሻ በማድረግ የሚሰሩ ሥራዎችን በመለየት በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞችን ወደ ሥራ ለማስገባት በሀገር አቀፍ ደረጃ መነሻ የሚሆን የቁርጥ ዋጋ አዘገጃጀት ማኑዋል ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፣
- ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶችን ተሞክሮ በመውሰድ የነጠላ ቁርጥ ዋጋ አተማመንና የኢንተርፕራይዞችን አደረጃጀት በመወሰን በሴክተሩ በፌደራልና ክልል ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት ወደ ተግባር እንዲገባ በማድረግ ለወጣቶችንለ ሴቶች በዘርፉ ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠር ልማትን ማፋጠን ነው፣

## የቀጠለ...

- በክልሉች ያሉ ተመሳሳይነት ያላቸው የግንባታ ስራዎች ወቅታዊ ዋጋዎች ተዳሰዋል፣
- በፌደራል የውሃ፣ የመስኖና የኢነርጂ ሚኒስቴር እና በክልል ውሃ ቢሮዎች የሚገኙ ስጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ የተለያዩ ዶክመንቶች (የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ፣ የውሃ ሀብት ልማት ስትራቴጂ ወዘተ...) ተፈትሸዋል፣
- በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዘርፍ ልምድ ያላቸውን የተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ዶክመንቶችን ማለትም የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ስትራቴጂ፣ የቁርጥ ዋጋ አዘገጃጀት ማንዋል ወዘተ... ተዳሰዋል፡፡

### የማንዋሉ ዓላማ

- በቁርጥ ዋጋ የሚዘጋጁ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሠሩ መጠጥ ውሃ ግንባታና የጥገና አገልግሎት ስራዎችን በመለየት ሥራ አጥ ወጣቶችን በዘርፉ አደራጅቶና አሰልጥኖ በማሰማራት በተቀላጠፈ መንገድ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት በተሞላበት የአሰራር ስርዓት በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ በሁለተኛው ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ዕቅድ ዘመን የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ሽፋንን ለማዳረስ ሰፊ ሥራ ለመሥራት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ልማት ዘርፍ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሊሰሩ የሚችሉ ሥራዎችን እና የአገልግሎት ዘርፎችን መለየት፣
- በተለዩት የሥራ መስኮች ላይ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል መጠን መወሰንና አጠቃላይ አደረጃጀቶችን መለየት፣
- የተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶችን ልምድ በመቀመር፣ የዘርፉን ተጨባጭ ሁኔታዎች ባገናዘበ መልኩና ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ የቁርጥ ዋጋ አዘገጃጀት ቀመር ማዘጋጀት፣

# የሚጠበቅ ውጤት

- ይህ የቁርጥ ዋጋ አዘገጃጀትና አደረጃጀት ማኑዋል በተለያዩ ክልሎች የመጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታ ሥራ ላይ ተሰማርተው ለሚሰሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያገለግል ሲሆን ይህም በተለያዩ ክልሎች የሚሰራበትን የዋጋ አተማመን ዘዴ አንድ ወጥ በማድረግ በአሰራር ላይ የሚታዩትን ችግሮች መፍታት ነው፡፡

## የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የደረጃ መለያ (Catagory)

- **ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ (Micro-Enterprise)፡-** ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ማለት ከ1 እስከ 5 ሰዎች እና የጠቅላላ ንብረታቸው /Total Asset/፡-
  - በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 ያልበለጠ፤
  - በኢንዱስትሪ/ኮንስትራክሽን/ ዘርፍ እስከ ከብር 100,000 ካፒታል ያለው ድርጅት ነው፡፡
- **አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ (Small Enterprise)፡-** የኢንተርፕራይዙን ከ6 እስከ 30 ሰዎች ተደራጅተው ጠቅላላ ንብረታቸው / Total Asset/ መጠን በዋጋ ሕንጻን ሳይጨምር: -
  - በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001 - 500,000 (ከግማሽ ሚሊዮን ብር) ያልበለጠ፤
  - በኢንዱስትሪ/ኮንስትራክሽን/ ዘርፍ ከብር 100,001 - 1,500,000 (ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር) ያልበለጠ ካፒታል ያለው ድርጅት ነው፡፡

# በጥ.ሰ.ሲ. የሚሠሩ ሥራዎች እንደሚከተለው ተለይቶዋል፡-

- ነባር የውሃ ተቋማት የማስፋፋት ሥራ፡-
  - የውሃ መስመር ዝርጋታ (Water Distribution-Line)
  - የውሃ ማጠራቀሚያ ፤ የቦኖ ግንባታ እና መሰል ሥራዎች (Water Reserviour, water point construction)
- አዲስ የውሃ ተቋማት ግንባታ ሥራ
  - ምንጭ ማጎልበት
  - ምንጭ በቦታው
  - ምንጭ ከመስመር ጋር
- የማከፋፈያ መስመር መዘርጋት
  - አነስተኛ የማከፋፈያ መስመር (Small Size Distribution Line)
  - መካከለኛ የማከፋፈያ መስመር (all Size Distribution Line)
  - የእጅ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ግንባታና ፓምፕ ተከላ
  - ሀንድ ኦገር ማንዋል ድሪሊንግ (Hand ouger manual drilling)
- የእጅ ጉድጓድ ግንባታ/ኮንክሪት ማምረት፤ ኮንክሪት ማስገባት፤ የአናት ሥራና የእጅ ፓምፕ ተከላ /Rope & Pump, like Afridev Pump/
  - የመስስተኛ ጥልቀ ጉድጓድ (Shallow well) ፓምፕ ተከላ /Like Afridev and Indian Mark II Installation/
  - በፀሐይና በንፋስ ኃይል የሚሠራ ፓምፕ ተከላ (Solar & wind-powered Pump Installation)

# የቀጠለ…

- የጣሪያ ላይ ውሃ ማሰባሰብ (Rain water harvesting)፤

  የአሸንዳ ሥራ እና የውሃ ማጠራቀሚያ እና ተዛማጅነት ያላቸው ሥራዎች፤
- ኩሬ

  የጣራ ውሃ፣ ዝናብ ወራጅ ውሃን በማሰባሰብ እና ወቅታዊ ጅረቶችን በማቀብ መሬት ላይ በመከተር –በመገደብ ውሃ በማከም ለአገልግሎት ማዋል ነው፡፡
- ቢርካ

  በተፋሰስ ውስጥ ያለ ወራጅ ውሃን በማሰባሰብ ከመሬት በታች ጉድጎድ ውስጥ ማጠራቀሚያ በመገንባት ውሃ በማከማቸትና በማከም ለአገልግሎት ማዋል ነው፡፡
- ሀፊርዳም

  በመሬት ላይ የሚፈስ ውሃ ለማቀብ በሸለቆ ላይ አግድም ቦይ በመቆፈር በአሸዋ የውሃ ማጠራቀሚያ ከመሬት በላይ ግድብ በመገደብ ውሃ በማቆርና በማከም ለአገልግሎት ማዋል ነው፡፡
- ሲስተርን

  ውሃ መቃጠር በሚያስችል ሁኔታ የሚገነባ የውሃ ማጠራቀሚያ ሲሆን የሚገነባውም የዝናብ ውሃ ለማጠራቀም ነው፡፡

# የጥገና አገልግሎት፣ የመለዋወጫ ፣ የኬሚካል አቅርቦትና ሽያጭ

የመለዋወጫ አቅርቦትና ሽያጭ፤ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚከናወኑ የጥገና ሥራዎች ናቸው

- በእጅ ፓምፖች ዙሪያ ማንኛውም ዓይነት የጥገና፣
- የውሃ መስመር ጥገና፣
- በውሃ ተቋማት የግንባታ ሥራ (civil works) እና መልሶ ግንባታ
- መስመር መዘርጋትና ጥገና እና
- የመለዋወጫ እና ኬሚካል አቅርቦትና ሽያጭ ሥራዎችና ወዘተ…ና ቸው፤

# የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አደረጃጀት

## ➢ የሰው ኃይል አደረጃጀት

- ኢንተርፕራይዞቹ በአባልነት ተደራጅተው በሥራው ሲሳተፉና የዘርፉን ልማት ሲያፋጥኑ የሚገባቸውም ባለሙያዎች እንዲሁ ተለይተዋል፡፡
- በዚህ መሠረት በአንድ ኢንተርፕራይዝ የተለያየ ሙያ ያላቸውና እንደሥራው አስፈላጊነት ቁጥራቸው እስከ 5 በጥቃቅን እና ከ6-30 በአነስተኛ ይደራጃሉ፣
- ሥራውንም የሚያስተባብር/የሚመራ አንድ ሥራ አስኪያጅ ይኖራቸዋል፡፡ ኢንተርፕራይዞቹ የሚደራጁት በወረዳ ደረጃ ሆኖ በወረዳው ይኖራሉ ተብሎ እንደሚገመተው የግንባታና ጥገና ፍላጎት መሠረት በማድረግ ኢንተርፕራይዞችን ማቋቋም ይቻላል፡፡

# በዘርፉ የሴቶችና ወጣቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

## በዘርፉ የሴቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

- እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በኢንተርፕራይዝ ከሚደራጁ አባላት መካከል 50 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡

## በዘርፉ የወጣቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

- ወጣቶችን በዘርፉ ማሳተፍ ያለው አስፈላጊነት ከፍተኛ ነው፡፡ ወጣቶች በሰፊው ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የሚደራጁ ባለሙያዎች

- አርቲዥያኖች/የሠለጠኑና ወደፊት የሚሠለጥኑ ሴላ የመተዳደሪያ ሥራ የሌላቸው ግንበኞችና አናጢዎች (4ኛ ክፍል ያጠናቀቁ)፣
- ከዩኒቨርሲቲዎች በዲግሪ እና በዲፕሎማ፣ ከቴክኒክና ሙያ ከኮሌጆች እና ማሠልጠኛ ተቋማት በዲፕሎማ እና ሰርቲፊኬት የተመረቁ፡-

## በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ በሚሰሩ ሥራዎች የሚደራጁ ባለሙያዎች አደረጃጀት

- የወረዳ ውሃ ጽ/ቤቶች ከወረዳው ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ጽ/ቤት ጋር በመሆን በውሃ ነክ ሥራዎች የሚደራጁትን ባለሙያዎች በመመዝገብና ምርጫ በማካሄድ፣ አባላቱን ለሥራው ብቁ የሚያደርግ የተሟላ ሥልጠና በክልል ውሃ ቢሮ፣ በዞንና በወረዳ ውሃ ጽ/ቤት በኩል እንዲያገኙ

## የሙያ ብቃት አሰጣጥ

- ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የግንባታ ፈቃድ ከደረጃው የሚጠይቀውን በማሟላት እውቅና ያገኛሉ፡፡

## ሥልጠና

- የተደራጁት አባላት በውሃ ሥራ ግንባታ ላይ ክህሎትና ልምድ ስለማይኖራቸው፤ ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት በመስኩ በዕቅድ ዝግጅት፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በተቋማት ግንባታ በኦፕሬሽንና ጥገና በሥራ ፈጠራ እና የንግድ በመሳሰሉት በቂ ሥልጠና መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡
- በክልሉ ውሃ ሀብት ቢሮ፣ በዞን ውሃ ማዕድንና ኢነርጂ መምሪያ፣ በወረዳ ውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ጽ/ቤት፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ እና እንደ አስፈላጊነቱ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ካላቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጠውን ስልጠና በሚገባ ሳጠናቀቁ ሰልጣኞች የምስክር ወረቀት በዞን/በወረዳ ውሃ ማዕድንና ኢነርጂ መምሪያ ጽ/ቤት በኩል ይሰጣል፡፡

# መሠረታዊ የዋጋ ትመና መርሆዎች

- ❖ **ዋጋ ትመና ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሁኔታዎች (Factors affecting price setting)**
  - ➢ **ውስጣዊ ተፅዕኖ** (internal factors)
    - የገበያ ዓላማ ፣ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የምርት ወጪዎች እና የአምራች ድርጅቱ አደረጃጀት
  - ➢ **ውጪያዊ ተፅዕኖ (External factors)**
    - የገበያና ባለው የምርት ፍላጎት ሁኔታ፣ የመንግስት ፍላጎት፣ ማህበረሰባዊ ምልከታ እና ሌሎችም

- ❖ **የቁርጥ ዋጋ አዘገጃጀት ለመጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታ**

አዲስ ለሚገነቡ የመጠጥ ዉሃ ተቋማት የቁርጥ ዋጋ ለማዘጋጀት መታየት ያለባቸዉ ነጥቦች፡-

- የፀደቀ ዲዛይን መሠረት በማድረግ የሥራ ዝርዝርና የቴክኒክ ፍላጎት መገለጫ ማዘጋጀት
- ለተዘጋጀው የሥራ ዝርዝር የዋጋ ዝርዝር ማዘጋጀት
- ዋጋዎችን ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ዋጋ ብሎ በሁለት መለየት
- ቀጥሎ የነጠላ ዋጋውን መወሰን ይህም
  - ➢ **የሥራ ነጠላ ዋጋ = ቀዋ + ቀያ +ት+ግ** (DC x O) + (DC x P)
  - ➢ **ማለትም** ቀዋ = ቀጥተኛ ዋጋ /Direct cost/

    ቀያ = ቀጥተኛ ያልሆነ ዋጋ = ቀዋ x 6% /Overhead cost/

    ት = ትርፍ = ቀዋ x 35%

    ግ = ግብር = ት x 10%

# ቀጥተኛ ዋጋ /Direct Cost (DC) / ስሌት

ቀዋ = ጥዕ+ ሠ + መሣ ማለትም

ጥዕ = የጥሬ ዕቃ ዋጋ 15 % ቫትን ያካተተ ይሆናል

ሠ = የሠራተኛ ዋጋ እና

መሣ = የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ዋጋ

## የጥሬ ዕቃ ዋጋ (ጥዕ )

- የጥሬ ዕቃ ዋጋ (ጥዕ) = መ × (ነዋ + ማማ + ማጓ) × ብ ማለትም
- መ= የጥሬ ዕቃ መጠን (በቴክኒካል ፍላጎት መግለጫውን መሠረት)
- ነዋ= የጥሬ ዕቃ ነጠላ ዋጋ (በቴክኒካል ፍላጎት መግለጫውን መሠረት በማድረግ የገበያ መረጃ በማሰባሰብ)
- ማማ = ማስጫኛና ማውረጃ
- ማጓ = ማጓጓዣ
- ብ = ብክነት

## ትርፍ (P)

- የፕሮጀክት ዋጋቸው ከ 35% የቀጥተኛ የሥራ ዋጋ /ወጪ/ ትርፍ ይሰላል፡፡

# የቀጠለ...

## የቁርጥ ዋጋ ክለሳ ሥነ-ስርዓት

- ወቅታዊ የሆነ የዋጋ ዝርዝር ግዢ ፈጻሚ መስሪያ ቤቱ በሚወክለው የተፈቀደለት አካል ይዘጋጃል፣
- ይህ የቁርጥ ዋጋ ወቅታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ ግዢ ፈጻሚ አካሉ በየስድስት ወሩ የዋጋ ክለሳ ሊያደርግ ይገባዋል ፣
- የተከለሰው የነጠላ ዋጋ ከሚመለከተው የበላይ አካል ይሁንታ ሳያገኝ አገልግሎት ላይ አይውልም፡፡

# ለጥገና አገልግሎትና ለመለዋወጫ አቅርቦት/ሽያጭ ቁርጥ ዋጋ አተማመን

## ለጥገና አገልግሎት የቁርጥ ዋጋ አተማመን

- የአንድ የውሃ ተቋም የጥገና አገልግሎት ዋጋ ተመና ለመስራት የሚከተሉት ነጥቦች ታሳቢ ሊደረጉ ይገባል፡-
  - ለአንድ ተቋም የጥገና ሥራ ለመሥራት የሚፈጀው ሰዓት
  - ለአንድ ሙያተኛ በሰዓት የሚከፈለው ክፍያ መጠን
  - ለጥገና ሥራው የሚያስፈልግ የሙያተኛ ብዛት
  - ጥገና የሚከናወንበት ተቋም ርቀት
- ሠዋ = (ዋሰ) x (1+ ሥጥ + ት) x (ጠሰ)

ሠዋ Cem = ለአንድ የጥገና ሰራተኛ የሚወጣ ወጪ (cost per employee)

ዋሰ = ሙያተኛው በሰዓት የሚከፈለው የክፍያ መጠን (Hourly labour rate)

ሥጥ = ከስራው ሊገኝ የሚገባ ጥቅም በመቶኛ (benefit ratio)

ት = የትራንስፖርት ወጪ (Transport cost)

ጠሰ = ጥገናው የሚፈጀው አጠቃላይ ሰዓት (Total number of maintenance hours)

ለጥገና ሥራ ለጠቅላላ ሠራተኛ የሚያስፈልግ ወጪ ፡-

ጠሠዋ = ሠዋ1+ ሠዋ2+ሠዋ3 … ወዘተ

ጠሠዋ = ጠቅላላ የሥራው ወጪ (total labor cost)

## መለዋወጫ ሽያጭ የቁርጥ ዋጋ ትመና ስሌት ቀመር

| መግለጫ | ምርመራ |
|---|---|
| የትራንስፖርት ወጪ (ት) | የመለዋወጫ ግዢ በሚከናወንበት ወቅት ለመለዋወጫዎች ማጓጓዣ የሚወጣ። |
| የሰራ ማስኬጃ ወጪ (ሥማ) | የደረሰኝ ማሳተሚያ፣ የፔትሮል፣ የስልክና መሰል ወጪዎች። |
| የትራንስፖርትና የሥራ ማስኬጃ ወጪ<br>ትሥማ = ት + ሥማ | ጠቅላላ የትራንሥፖርትና የሥራ ማስኬጃ ወጪ ድምር። |
| በዓመት ወስጥ ይሸጣሉ ተብሎ የሚጠበቅ የመለዋወጫዎች ብዛት (ብ) | በዓመት ውስጥ ሊሸጡ የሚችሉ መለዋወጫዎች ብዛት። |
| ለአንድ መለዋወጫ የትራንስፖርትና የሥራ ማስኬጃ ወጪ ትሥማአ = ትሥማ/ብ | ለአንድ መለዋወጫ የሚወጣ የትራንስፖርትና የሥራ ማስኬጃ ወጪ ። |
| የመለዋወጫዎች መግዣ ነጠላ ዋጋ (ዋ) | አንድ መለዋወጫው የተገዛበት ነጠላ ዋጋ። |
| መሠረታዊ መሸጫ ዋጋ መዋ = ትሥማአ+ዋ | ትርፍና መጠባበቂያ ሳይጨምር የመለዋወጫ መሸጫ ዋጋ። |
| መጠባበቂያ (መጠ) | የመሠረታዊ መሸጫ ወጪ 10 በመቶ በታሳቢነት የሚያዝ። |
| መጠባበቂያ ጨምሮ መሠረታዊ መሸጫ ዋጋ መመዋ = መዋ + መጠ | መለዋወጫ ጠቅላላ ወጪንና መጠባበቂያ ሸፍኖ ያለ ትርፍ የሚሸጥበት ዋጋ። |
| የትርፍ ስሌት ጠቅላላ መሠረታዊ መሸጫ ዋጋ 15 በመቶ ይሆናል | መጠባባቂያ ጨምሮ ጠቅላላ መሰረታዊ መሸጫ ዋጋ 15 በመቶ |
| ትርፍ ትፍ = መመዋ x 0.15 | መሰረታዊ መሸጫ ዋጋ 15 በመቶ። |
| ትርፍና ታክስ (ታግ) | መሰረታዊ መሸጫ ዋጋ 15 በመቶ ግብር። |
| **የአንድ መለዋወጫ ዋጋ መዋአ = ትፍ + ታግ** | መጠባበቂያ፣ ትርፍና ግብርን ጨምሮ ነጠላ መለዋወጫ ዋጋ |

# የማነዋሉ አተገባባር

- ማንዋሉን ለመተግበር የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ አሰራር ይጠይቃል፡፡ በዚሁ መሠረት የዚህ ማንዋል ዋንኛ ተግባሩ የሚሆነው የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዳይሬክቶሬት ነው፡፡ ይህንን ሥራ ለማከናወን ዳይሬክቶሬቱ ሌሎች ባለድርሻ አካላትን አስተባባሪ በተሰጣቸው የሥራ ተግባርና ኃላፊነት መሠረት እንዲሰሩ በማስተባበር ሥራውን ማከናወን ይገባዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ተለይቶአል፡፡

## ባላድርሻ አካላቱም እንደሚከተለው ተለይተዋል:-

- የውሃ፣ መስኖና ኢሌክትሪክ ሚኒስቴር፤
- የክልል ውሃ ሀብት ልማት ቢሮዎች፤
- የክልል ጥ/አ/ኢ/ ኤጀንሲዎች፤
- የዞንና የወረዳ ውሃ ሀብት ልማት መምሪያና ጽ/ቤቶች፤
- የዞንና የወረዳ ጥ/አ/ኢ/ል/ መ/ቤቶች፤
- የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት፤
- በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ሥራዎች የሚደራጁት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፤
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣
- የውሃ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው እና
- በየደረጃው የሚገኙ የሴቶችና ወጣቶች ጽ/ ቤቶች ናቸው፡፡

# አባሪዎች

**አባሪ 1**

**የጥቃቅንና ነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የውሃ ሥራዎች ግንባታ ሥራ**

- የኢንተርፕራይዝ ደረጃ መለያ ደረጃ 1 ጥቃቅን
  - 1 – 5 የሰው ኃይል ያለው
  - እስከ ብር 100000
  - የተዘረዘሩ የሚሠሩ ሥራ ዓይነቶች እና ማሚላት ያለበት መስፈርት በሰው ኃይልና በካፒታል
- የኢንተርፕራይዝ ደረጃ መለያ ደረጃ 2 አነስተኛ – 1
  - 6 – 15 የሰው ኃይል ያለው
  - እስከ ብር 100001 – ብር 500000
  - የተዘረዘሩ የሚሠሩ ሥራ ዓይነቶች እና ማሚላት ያለበት መስፈርት በሰው ኃይልና በካፒታል
- የኢንተርፕራይዝ ደረጃ መለያ ደረጃ 2 አነስተኛ – 2
  - 16 – 30 የሰው ኃይል ያለው
  - እስከ ብር 500001 – ብር 1500000
  - የተዘረዘሩ የሚሠሩ ሥራ ዓይነቶች እና ማሚላት ያለበት መስፈርት በሰው ኃይልና በካፒታል

**አባሪ – 2**

**የጥቃቅንና ነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የውሃ ሥራዎች ግንባታ ሥራ የመሣሪያዎች ዝርዝርና ብዛት ለጥቃቅን፣ ለአነስተኛ – 1 እና ለአነስተኛ – 2 የተለየበት፣**

## ሰባዊ 3

## የጥቃቅንና ነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዋጋን መሠረት ያደረገ የውሃ ነክ ሥራዎች ሥራ ተቋራጭደረጃ አወሳሰን መሥፈርት፡-

| ተ. ቁ | የኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት ደረጃ መለያ | የኢንተርፕራይዞች ትርጓሜ | መነሻ ካፒታል (ብር) | የግንባታ ዋጋ ጣራ (ብር) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ | ከ1-5 ሰው እና ከብር 100000 ካፒታል ያለው ድርጅት | 20000 | እስከ 250000 |
| 2 | አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ | ከ6-15 ሰው እና ከብር 100001-500000 ካፒታል ያለው ድርጅት | 100001 | እስከ 1 ሚሊዮን |
| 3 | | ከ16-30 ሰው እና ከብር 500000-1500000 ካፒታል ያለው ድርጅት | 500001 | እስከ 10 ሚሊዮን |

## ዋቢ መጽሐፍት

ይህንን ማንዋል ለማዘጋጀት 10 የሚሆኑ የተለያዩ ፡- ስትራቴጂ፣ መመሪያዎች፣ በዘርፉ የተጣፉ መጽሐፎች፣ ፓኬጅእና ማንዋሎች ተዳሰዋል፡፡

## የተፈፃሚነት ወሰን

- ይህ የቁርጥ ዋጋ አዘገጃጀት ማንዋል የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ የክልል ውሃ ሀብት ቢሮዎች፣ የዞንና የወረዳ ውሃ ጽ/ቤቶች እንዲሁም በሴክተሩ የተሰማሩ የልማት አጋሮች ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

አመሰግናለሁ!